

# ትንሽ ተነቃነቅ...



ላብህ ተንጠፍጥፎ ደምህ ነጥፎ ሳትደርቅ፣
እንደ ሰብ ሰው ሆነህ ትንሽ ተነቃነቅ፣
ቁንጫ ሲበላው ሰው ይገላበጣል፣
ራሱን ይላጫል ልብሱን በንዶድ ያጥባል፣ መዳኒት ይረጫል፣
በመነቃነቁ ተባዩን አጥፍቶ እፎይ ብሎ ያርፋል።
እ'ሱ ያመጣውን እ'ሱ እስኪመልሰው እያለ የተኛ፣
መፍትሄ የሌለው ህልም-አልባ ህልመኛ፣
አንዱ ሲነቃነቅ መተቸቱን ትተህ
አንተም ተነቃነቅ ፈሪን ታስፈራለህ
ገንዘብ ሲሉህ አውጣ ከበሉትም ይብሉት፣
ደም ይሁንባቸው ይህን ለፈፀሙት፣
ስብሰባ ሲጠሩ ሄደህ ተቀላቀል፣
ሳታይ ሳትሰማ አታውርድ አትስቀል
አንተም አንችም እኔም ሁላችንም ሆነን፣
ከተነቃነቅን ተአምር እንሰራለን፣ አጥፊ እናጠፋለን።
ምነው ያገሬ ሰው ቆለኛ ደገኛ፣
ቁጭ በል ተኛ ሲሉህ እንደ በሽተኛ፣
መፍትሄ የነበርከው የአስማቱ መለኛ፣
እሳት መሀል ነዷል በልጦህ ከተሜኛ፣
ስማቸውን ጥራ የ'ናት ያ'ባትህን ወደላይ ያ'ያትህን፣
እንደገና ሞተው ቀንበሩን ያንሱልህ የተሸከምከውን፣
አንተን እነዳትጠራ በስምህ እንዳትምል ማንም አያውቅህም፣
በ “አኮ-ሰብዕ” መገዛት ገና አልሰለቸህም፣
ጊዜ ዘመን ቆጥሮ እንደቆምክ ሳትወድቅ፣
ታሪክ ልስራ ብለህ ትንሽ ተነቃነቅ።

ታህሳስ 2002 ዓ/ም
ወርቅእሸት ቸርነት



